የሰ/መ/ቁ. 61872

የካቲት 10 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ሐጐስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

*አመልካች፣* የኢትዮጵያ ፐልፐና ወረቀት አ/ማ ታፈሰ አበበ ቀረበ

*ተጠሪ፣* ዓብዱልቃድር አደም ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳውን የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በአመልካች ፋብሪካ ለ38 /ሰላሳ ስምንት/ ዓመት ካገለገልኩ በኃላ ለጡረታ አራት /4/ ዓመት ሲቀረኝ በራሴ ፍላጎት ሥራውን የለቀቅሁ በመሆኑ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ነው አመልካችም በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ሊሟላ የሚገባው ሁሉ ተሟልቶለት ጡረታ የወጣ በመሆኑ የስንብት ክፍያ ሊከፈለው አይገባም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ አይፈቅድለትም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኃላ ፍ/ቤት ክርክሩን የመረመረ ሲሆን በመቀጠልም የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ተጠሪ የሥራ ስንብት ይከፈለው በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ ከተሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አፅንቶአል፡፡ በመጨረሻው የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት አይደለም በማለት አቤቱታውን ሰርዞአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ጥቅምት 29 ቀን 2003 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈለው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ 377/96ን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ 494/98 በአንቀጽ 2 ከተመለከተው ድንጋጌ አንፃር ሊመረመር የሚገባው ነው በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ በራሱ ፍላጎት የሥራ ውሉን ያቋረጠው /ከሥራ የተሰናበተው/ 38 /ሰላሳ ስምንት/ ዓመት ካገለገለ በኃላ እንዲሁም ዕድሜው 60 /ስድሳ/ ዓመት ሊሞላ 4 /አራት/ ዓመት ሲቀረው እንደሆነ አላከራከረም የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለኝ ይገባል የሚለው በእርግጥም በአሁኑ ጊዜ

የጡረታ አበል አላገኝም /አይከፈለኝም/ በማለት ሳይሆን ሥራውን በራሴ ፍላጎት በመለቀቄ እና በሕጉ የተመለከተውን የመጨረሻ የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት ስላልሞላኝ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለኝ በማለት እንደሆነም ከክርክሩ ይዘት ተገንዝበናል አመልካች ደግሞ ተጠሪ ሥራውን የለቀቀው /የተሰናበተው/ ሊሟላለት የሚገባው ሁሉ ተሟልቶለት በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የጡረታ አበል እየተከፈለው ነው፡፡ የጡረታ አበል የሚያገኝ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያም እንዲከፈለው ሕጉ አያዝም ይልቁንም ሁለቱ ክፍያዎች በአንድ ጊዜ እንዳይከፈሉ ሕጉ በግልፅ ይከለክላል በማለት ተከራክሮአል፡፡

እንደምንመለከተው አከራከሪው ጭብጥ የሕግ ነጥብ በመሆኑ ሊፈታ የሚችለው አግባብ ባለው የሕጉ ድንጋጌ ነው፡፡ ክርክሩ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሳ በመሆኑም በቅድሚያ መታየት ያለበት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 ነው በዚህ አዋጅ ስለሥራ ስንብት ክፍያ በሚመለከት ተደንግጎ የሚገኘው በአንቀጽ 39 ሲሆን ይህ ድንጋጌ አዋጁን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 494/98 ተሻሽሎአል፡፡ በዚህ ማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 2/ሰ/ እና /ሸ/ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተጣምረው ሲታዩ አንድ ከሥራው የተሰናበተ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚከፈለው በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከሥራው በሚገለልበት ጊዜ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ሲሆን ወይም ደግሞ ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ በሕመም ወይም በፈቃዱ ሲለቅ /ሥራው ላይ የሚያስቀይ ከሥልጠና ጋር የተያያዘ የውል ግዴታ ሳይኖርበት የለቀቀ ሲሆን/ እንደሆነ ነው በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ሥራውን የለቀቀው በገዛ ፈቃዱ ሲሆን እንደለቀቀም በጡረታ መብት ተጠቃሚ ሆኖአል፡፡ በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀጽ 13/3/ እንደተመለከተው ቢንያስ ሃያ አምስት ዓመት ያገለገለ የመከላከያ ሠራዊት አባል ያልሆነ የመንግስት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ  ጀምሮ እስከ ዕድሜ ልኩ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡ ተጠሪ ሥራውን በራሱ ፈቃድ የለቀቀው 60 ዓመት ሊሞላው 4 ዓመት ሲቀረው በመሆኑ በዚህ ሕግ መሠረት አበሉን እያገኘ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡

ከፍ ሲል በዝርዝር እንዳመለከትነው የጡረታ አበል እና የሥራ ስንብት ክፍያ አንድ ላይ እንዲከፍሉ ሕጉ አልፈቀድም፡፡ ሕጉ ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ከሕጉ መውጣት የሚቻል አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንደምናየው ሕጉን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ ይልቁንም ሕጉን በግልጽ በሚቃረን መልክ የተሰጠ ሆኖ ነው ያገኘነው፡፡ ከዚህ የተነሳም አቤቱታው የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 39748 ሰኔ 11 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 25367 ጥቅምት 17 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ 116497 ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሸረዋል፡
2. ተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ የሚያገኝበት የሕግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡  መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

ም.አ *የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት*